# ትምህርት 31

1. እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከግብፅ ካወጣቸው በኋላ ወደ የትኛው ምድር መራቸው?

ሀ- መልሶ ወደ ከነዓን ምድር መራቸው።

2. እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በቀን የመራቸው እንዴት ነበር?

ሀ- በደመና ዓምድ።

3. እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በሌሊት የመራቸው እንዴት ነበር?

ሀ- በእሳት ዓምድ።

4. እግዚአብሔር እስራኤላውንን እስከ ቀይ ባሕር ዳርቻ ድረስ የመራቸው ለምን ነበር?

ሀ- እግዚአብሔር እርሱ ብቻ አምላክ መሆኑን ግብፃውያንም ሆኑ እስራኤላውያን እንዲያውቁ ስለ ፈለገ።

5. እስራኤላውያን ፈርዖንና ጦሩ መልሰው ሊይዟቸው እንደ መጡ ሲያዩ ምን አደረጉ?

ሀ- እስራኤላውያን ሙሴን ነቀፉት በግብፅ መቆየት ይሻላቸው እንደ ነበር ነገሩት።

6. እስራኤላውያን ራሳቸውን ማዳን ችለው ነበር?

ሀ- አልቻሉም።

7. እስራኤላውያን ራሳቸውን ማዳን ያልቻሉት ለምን ነበር?

ሀ- ምክንያቱም ቀይ ባሕር ከፊት ለፊታቸው ተራሮች በቀኝና በግራቸው እንዲሁም ደግሞ የፈርዖን ሠራዊት ከኋላቸው ስለነበር ነው።

8. እስራኤላውያንን ማዳን የቻለው ማን ብቻ ነበር?

ሀ- እግዚአብሔር።

9. ቀይ ባሕርን መክፈል ለእግዚአብሔር አስቸጋሪ ያልሆነው ለምን ነበር?

ሀ- ምክንያቱም ቀይ ባሕርን የፈጠረው እግዚአብሔር ስለሆነ ነው።

ለ- ምክንያቱም የባሕሩ ሁሉ ጌታ እግዚአብሔር ስለሆነ ነው።

ሐ- ምክንያቱም እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ስለ ሆነ ሁሉን ማድረግ ለሚችል ነው።

10. ፈርዖንና ሠራዊቱ እስራኤላውያንን መልሰው ለመያዝ በመምጣት ላይ ነበሩ፤ እስራኤላውያንን ለመከላከል እግዚአብሔር ምን አደረገ?

ሀ- እግዚአብሔር በእስራኤላውያንና በፈርዖን ሠራዊት መካከል ደመናን አደረገ።

ለ- ደመናው ለእስራኤላውያን ብርሃን ሲሰጥ ለፈርዖንና ለሠራዊቱ ግን ጨለማ እንዲሆን አደረገ።

11. ፈርዖንና ሠራዊቱ እስራኤላውያንን ተከታትለው ወደ ቀይ ባሕር ሲገቡ እግዚአብሔር ምን አደረገ?

ሀ- እግዚአብሔር ፈርዖንና ሠራዊቱን በቀይ ባሕር ውስጥ አሰመጣቸው።

12. እግዚአብሔር እስራኤላውያንን የጠበቃቸው ለምንድን ነው?

ሀ- እግዚአብሔር እስራኤላውያንን የጠበቃቸው ከአብርሃምና ከእስራኤላውያን ዘር አዳኝ እንደሚልክ ቃል ስለ ገባ ነው።

ለ- እግዚአብሔር እስራኤላውያንን የጠበቃቸው ደግሞ፥ ቃሉን ማለትም መጽሐፍ ቅዱስን በአብርሃምና በእስራኤላውያን አማካይነት ወደ ዓለም ሕዝቦች ሁሉ ለመላክ ስለ ፈለገ ነው።

- እግዚአብሔር ፈርዖንንና ሠራዊቱን በቀይ ባሕር ውስጥ ከደመሰሳቸው በኋላ እስራኤላውያንን ወዴት መራቸው?

- ወደ ምድረ በዳ።

- ምድረ በዳ ምንድን ነው?

- ምድረ በዳ አሸዋ ብቻ ያለበት ምድር ነው።

- በምድረ በዳ ዐፈር የለም።

- በምድረ በዳ ሣር የለም።

- በምድረ በዳ ዛፎች የሉም።

- በምድረ በዳ ያለው አሸዋ ብቻ ነው።

- እግዚአብሔር በምድረ በዳ እየመራቸው ሳለ እስራኤላውያን ምን አደረጉ?

ዘጸአት 16፡1-3

1- መላው የእስራኤል ማኅበር ከግብፅ በወጡ በሁለተኛው ወር ከወሩም በአሥራ አምስተኛው ቀን ከኤልም ተነሥተው በኤልምና በሲና መካከል ወደምትገኘው ወደ ሲን ምድረ በዳ መጡ።

2- በምድረ በዳውም መላው ማኅበር በሙሴና በአሮን ላይ አጉረመረሙ።

3- እስራኤላውያንም እነርሱን እንዲህ አሏቸው፣ «በሥጋ መቀቀያው ምንቸት ዙሪያ ተቀምጠን የፈለግነውን ያህል ምግብ መመገብ በምንችልበት በግብፅ ሳለን፣ ምነው በእግዚአብሔር እጅ ሞተን ባረፍነው ኖሮ! እናንተ ግን ይህ ሁሉ ጉባኤ በራብ እንዲያልቅ ወደዚህ ምድረ በዳ አመጣችሁን» አሏቸው።

- እስራኤላውያን ሙሴንና አሮንን ነቀፉ።

- እስራኤላውያን ሙሴንና አሮንን የነቀፉአቸው ለምን ነበር?
- ምንም ምግብ ስላልነበራቸው።

- እስራኤላውያን ምግብ ያጡት በምን ምክንያት ነበር?

- በምድረ በዳ ምንም ምግብ ባለመኖሩ።
- በምድረ በዳ ያለው አሸዋ ብቻ ነበር።

- ሙሴ በምድረ በዳ ለእስራኤላውያን ምግብ ማግኘት ችሎ ነበር?
- አልቻለም።

- ሙሴ በምድረ በዳ ለእስራኤላውያን ምግብ ማግኘት ያልቻለው ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም በምድረ በዳ ምንም ምግብ ባለመኖሩ ነው።

- እስራኤላውያን በምድረ በዳ ለራሳቸው ምግብ ማግኘት ችለው ነበር?
- አልቻሉም።

- ለምን አልቻሉም?
- ምክንያቱም በምድረ በዳ ምንም ምግብ ባለመኖሩ ነው።

- ለእስራኤላውያን በምድረ በዳ ምግብ መስጠት የቻለው ማን ብቻ ነበር?
- እግዚአብሔር።

- እስራኤላውያን እግዚአብሔር በምድረ በዳ ምግብ እንደሚሰጣቸው አምነው ነበር?

- አላመኑም።

- እስራኤላውያን እግዚአብሔር በምድረ በዳ ምግብ እንደሚሰጣቸው ከማመን ይልቅ ምን አደረጉ?

- ሙሴንና አሮንን ነቀፉአቸው።

- እግዚአብሔር እስራኤላውያን ሙሴንና አሮንን እንደ ነቀፉ ሰምቶአቸዋል?

- አዎን።

- እግዚአብሔር ሙሴን ምን አለው?

ዘጸአት 16፡11-12

11- እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ አለው፤

12- «የእስራኤላውያንን ማጉረምረም ሰምቻለሁ፤ ይህን ንገራቸው፤ ፀሐይ ከመጥለቋ በፊት ሥጋ ትበላላችሁ፤ ሲነጋም እንጀራ ትበላላችሁ፤ ከዚያም እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ መሆኔን ታውቃላችሁ።»

- እግዚአብሔር ሙሴን «ለእስራኤላውያን ምግብ እሰጣቸዋለሁ» አለው።

- እስራኤላውያን በእግዚአብሔር ባያምኑም እንኳ እርሱ ለእነርሱ «ምግብ እሰጣቸዋለሁ» አለ።

- እስራኤላውያን በእርሱ ላይ እምነት ባይኖራቸውም እንኳ እግዚአብሔር እነርሱን ይረዳቸው ነበር።

- ሰዎች ባያምኑትም እንኳን፥ እግዚአብሔር የሚረዳቸው ለምንድን ነው?

- ምክንያቱም እግዚአብሔር ሁሉንም ሰው ስለፈጠረ ነው።

- ምክንያቱም እግዚአብሔር ሁሉንም ሰው ስለሚወድ ነው።
- ምክንያቱም እግዚአብሔር ሁሉንም ሰው ማዳን ስለሚፈልግ ነው።

- ምክንያቱም እግዚአብሔር ሁሉም ሰው እንዲያምንበት ስለሚፈልግ ነው።

- እኛ በእግዚአብሔር ካላመንን እግዚአብሔር ያድነናል?
- አያድነንም።

- እግዚአብሔር እስራኤላውያን በረሃብ እንዲያልቁ አድርጓልን?
- እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ምግብ ሰጥቷልን?

ዘጸአት 16፡13

13- በዚያች ምሽት ድርጭቶች መጥተው ሰፈሩን አለበሱት።

- እግዚአብሔር በዚያች ምሽት በበረሃ ሳሉ ለእስራኤላውያን የሰጣቸው ሥጋ ምን ነበር?

- ድርጭቶች።

- የእስራኤላውያንን ሠፈር የሸፈኑ እጅግ በጣም ብዙ ድርጭቶች ነበሩ።

- በቀጣዩ ማለዳ እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ብዙ ምግብ ሰጣቸው።

## ዘጸአት 16፥13ለ-15 & 31

13- በነጋውም በሰፈሩ ዙሪያ ጤዛ ተኝቶበት ነበር።

14- ጤዛው ከረገፈ በኋላ፣ በሜዳው ላይ ስስ የሆነ አመዳይ የሚመስል የተጋገረ ነገር በምድረ በዳው ላይ ታየ።

15- እስራኤልውያንም ይህን ባዩ ጊዜ፣ ምን እንደ ሆነ ባለማወቃቸው እርስ በርሳቸው «ይህ ነገር ምንድን ነው?» ተባባሉ። ሙሴም፣ «ይህ ትበሉት ዘንድ እግዚአብሔር የሰጣችሁ እንጀራ ነው» አላቸው።

31- የእስራኤልም ሕዝብ ምግቡን መና አሉት። እርሱም እንደ ድንብላል ዘር ነጭ፣ ጣሙም ከማር እንደ ተጋገረ እንጀራ ነበር።

- እግዚአብሔር በሚቀጥለው ቀን ለእስራኤላውያን የሰጣቸው ምግብ ምን ነበር?

- እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን እንጀራ ሰጣቸው።

- እንጀራው ሰፈራቸውን በሙሉ ሸፍኖት ነበር።

- እግዚአብሔር ከሰማይ ያወረደላቸውን እንጀራ እስራኤላውያን ምን ብለው ሰየሙት?

- መና።

- በየማለዳው እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ለመመገብ እንጀራን እንደ ጤዛ ይልክላቸው ነበር።

- በየማለዳው እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ከሰማይ ያወረደላቸው መና የእግዚአብሔር ጸጋ ምልክት ነበር።

- አዳምና ሔዋን በእግዚአብሔር ላይ ቢያምፁም እግዚአብሔር በጸጋው እኛን ለማዳን አዳኝ እንደሚልክ ቃል ገባ።

- ኖኅና ቤተሰቡ ኃጢአተኞች ቢሆኑም እግዚአብሔር በጸጋው ከጥፋት ውኃ ጠበቃቸው።

- እስራኤላውያን በእግዚአብሔር ባያምኑም እግዚአብሔር በጸጋው ከግብፅ ባርነት አዳናቸው።

- እስራኤላውያን እግዚአብሔር ሊያድናቸው እንደሚችል ባያምኑበትም እንኳ እግዚአብሔር በጸጋው ቀይ ባሕርን ከፍሎ ከፈርዖንና ከግብፃውያን ሠራዊት አስመለጣቸው።

- እነዚህ በሙሉ የእግዚአብሔር ጸጋ ምልክቶች ናቸው።

- እስራኤላውያን በምድረ በዳ በነበሩባቸው ጊዜያት ሁሉ እግዚአብሔር በየቀኑ መና ይሰጣቸው ነበር።

ዘጸአት 16፥35

35- እስራኤላውያን ወደ መኖሪያቸው ምድር እስኪመጡ ድረስ ለአርባ ዓመት መና በሉ፤ ወደ ከነዓን ድንበር እስከሚደርሱ ድረስ መና በሉ።

- እግዚአብሔር አንድም ቀን ለእስራኤላውያን መና መስጠትን ረስቶ አያውቅም።

- እግዚአብሔር የገባውን ቃል ምንጊዜም ይጠብቃል።

- እግዚአብሔር ድርጭትና መና ለእስራኤላውያን ቢሰጣቸውም እስራኤላውያን እንደገና አጉረመረሙ።

ዘጸአት 17፥1-4

1- መላው የእስራኤል ማኅበር ከሲና ምድረ በዳ ተነሥቶ እግዚአብሔር እንዳዘዘው ከስፍራ ወደ ስፍራ ተጉዘው በራፊዲም ሰፈሩ፤ ነገር ግን ሕዝቡ የሚጠጡት ውኃ አልነበረም።

2- ስለዚህ፣ የምንጠጣው ውኃ ስጠን በማለት ሙሴን ተጣሉት። ሙሴም፣ «እኔን ለምን ትጣሉኛላችሁ? እግዚአብሔርንስ ለምን ትፈታተናላችሁ?» አለ።

3- ነገር ግን ሕዝቡ በዚያ ተጠምተው ስለነበር፤ በሙሴ ላይ አጉረመረሙ። እነርሱም፣ እኛና ልጆቻችን እንዲሁም ከብቶቻችን በውኃ ጥም እንድናልቅ፣ ከግብፅ ለምን አወጣኸን?» አሉት።

4- ከዚያም ሙሴ፣ «በዚህ ሕዝብ ላይ ምን ላድርግ? በድንጋይ ሊወግሩኝ ተዘጋጅተዋል» ብሎ ወደ እግዚአብሔር ጮኸ።

- እስራኤላውያን ያጉረመረሙት ለምን ነበር?
- ምንም ውኃ ስላልነበራቸው ነው።

- እስራኤላውያን ምንም ውኃ ያልነበራቸው ለምን ነበር?

- ምክንያቱም እነርሱ በምድረ በዳ ስለነበሩ ነው።
- ምክንያቱም በምድረ በዳ ምንም ውኃ ባለመኖሩ ነው።

- ሙሴ በምድረ በዳ ለእስራኤላውያን ውኃ መስጠት ችሎአል?
- አልቻለም።

- ለምን አልቻለም?
- ምክንያቱም በምድረ በዳ ውስጥ ምንም ውኃ ባለመኖሩ ነው።

- እስራኤላውያንስ ለራሳቸው በምድረ በዳ ውስጥ ውኃ ማግኘት ችለው ነበር?

- አልቻሉም።
- ለምን አልቻሉም?

- ምክንያቱም በምድረ በዳ ውስጥ ምንም ዓይነት ውኃ ባለመኖሩ ነው።

- በምድረ በዳ ውስጥ ለእስራኤላውያን ውኃ መስጠት የቻለው ማን ብቻ ነው?
- እግዚአብሔር።

- እስራኤላውያን እግዚአብሔር በምድረ በዳ ውኃ እንደሚሰጣቸው አመኑ?
- አላመኑም።

- በምድረ በዳ እግዚአብሔር ውኃ እንደሚሰጣቸው ከማመን ይልቅ እስራኤላውያን ምን አደረጉ?

- ሙሴንና አሮንን ነቀፉ።

- እስራኤላውያን ሙሴንና አሮንን እንደ ነቀፉ እግዚአብሔር ሰምቷል?
- አዎን።

- እግዚአብሔር እስራኤላውያን በጥም እንዲሞቱ አድርጓል?
- እግዚአብሔር ሙሴን ምን አለው?

ዘጸአት 17፥5-6ሀ

5- እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲህ መለሰለት፣ «ከሕዝቡ ፊት ሄድ፤ ከእስራኤል አለቆች አንዳንዶቹን እንዲሁም አባይን የመታህባትን በትር ያዝና ሂድ።

6- ኮሬብ አጠገብ ባለው ዐለት በዚያ እኔ በአንተ ፊት እቆማለሁ። ዐለቱን ምታው፤ ከእርሱም ሕዝቡ የሚጠጡት ውኃ ይወጣል።»

- እግዚአብሔር ሙሴ ውኃን ለማግኘት ምን እንዲያደርግ ነገረው?
- እግዚአብሔር ሙሴ በበትሩ ዓለቱን እንዲመታ አዘዘው።

- ሙሴ እግዚአብሔርን ከታዘዘ እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ውኃ ይሰጣቸዋል።

- ለእስራኤላውያን ከዐለት ውስጥ ውኃ ማፍለቅ የቻለው ማን ብቻ ነበር?
- እግዚአብሔር።

- ሙሴ እግዚአብሔርን ታዟል?

ዘጸአት 17፥6ለ

6- ስለዚህ ሙሴ በእስራኤል አለቆች ፊት ይህንኑ አደረገ።

- ሙሴ እግዚአብሔርን ታዘዘ።
- ሙሴ ልክ እግዚአብሔር እንደ ተናገረው በበትሩ ዐለቱን መታው።

- ሙሴ እግዚአብሔርን ስለ ታዘዘ እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ውኃ ሰጣቸው።

- እግዚአብሔርን ስንታዘዝ እግዚአብሔር ያድነናል።

- በእግዚአብሔር ላይ ስናምፅ እግዚአብሔር አያድነንም።
- እግዚአብሔርን ልንታዘዝ የሚገባን እርሱ በሚፈልገው መንገድ ነው።

- እኛ እግዚአብሔርን በራሳችን መንገድ ልንታዘዘው አንችልም።

- በራሳችን መንገድ ከሄድን እግዚአብሔ አያድነንም።
- እግዚአብሔር ሊያድነን የሚችለው በእርሱ መንገድ ከሄድን ብቻ ነው።

- ከኃጢአት ኃይል ሊያድነን የሚችለው ማን ብቻ ነው?
- እግዚአብሔር ብቻ።

- ከሞት ኃይል ሊያድነን የሚችለው ማን ብቻ ነው?
- እግዚአብሔር ብቻ።

- ከሰይጣን ኃይል ሊያድነን የሚችለው ማን ብቻ ነው?
- እግዚአብሔር ብቻ።

- እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ያዳናቸው እነርሱ በወሰኑት መንገድ ነው?
- አይደለም።

- እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ያዳናቸው እንዴት ነበር?
- እግዚአብሔር በወሰነው መንገድ ነው።

- እግዚአብሔር ሰዎችን ሁሉ የሚያድነው እንዴት ነው?
- እግዚአብሔር ራሱ በወሰነው መንገድ ነው።